# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

## አንደኛ እሑድ ዘክረምት - የክረምት የመጀመሪያ እሑድ

ከሰኔ ፳፭ እስከ ሐምሌ ፲፭ ቀን ድረስ በዐተ ክረምት (የክረምት መግባት) ይባላል። ሥርዓተ አምልኮውም የተመሰረተው ወቅቶችን ስለሚለውጠው አምላክ ኃይል፣ ስለ ደመናዎች፣ ስለ ዘር፣ እግዚአብሔር በኃውን አሳልፎ ክረምቱን ስለማምጣቱ፣ ደረቁን ስለማለምለሙ በሚያስታውሱ ክፍላተ መጽሐፍት ላይና መዝሙራት ላይ ነው። በተጨማሪም በክረምት ነገረ ትንሣኤ ይሰበካል፤ የዘሩ መዘራት እንደ መሞት መቀበር፤ መብቀሉ ደግሞ እንደ መነሳት ይወሰዳል። በምሳሌ ይሰበካል ክረምት ቢዘገይም እንደማይቀር ምጽአትም ሞትም እይቀሩምና በንጽጽር ይሰበካል።

### የዕለቱ ምስባክ

ዘይገለብቦ ለሰማይ በደመና
ወያስተዴሉ ክረምተ ለምድር
ዘያበቊል ሣዕረ ውስተ አድባር

ሰማይን በደመናት የሚሸፍን እርሱ ነው
ለምድርም ዛናምን ይሰጣል
በተራሮችም ላይ ሣር ያበቅላል።

መዝ ፩፻፵፮፥፰

ወንጌል፥ ሉቃስ ፰፥፩-፲፭
ቅዳሴ፥ የኤጲፋንዮስ (ዐቢይ) ቅዳሴ

### የዕለቱ የቅዱስ ያሬድ መዝሙር ርዕስ

ደምፀ እገሪሁ ለዝናም ... «የዝናም ኮቴው ተሰማ ...»

### በቅዳሴ ሰዓት የሚነበቡ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች

| | ንባብ | አንባቢ |
|---|---|---|
| 1 | ፩ኛ ቆሮ ፲፭፥፴፭-፶፩ | ዲያቆን (ገባሬ ሰናዩ) |
| 2 | ያዕ ፭፥፲፯-ፍጻሜ | ዲያቆን (ንፍቅ ዲ.) |
| 3 | የሐዋ ሥራ ፳፯፥፲፩-፳፩ | ረዳቱ ቄስ (ንፍቅ ካህን) |

### የዕለቱ ትምህርት

## ዘሪ ሊዘራ ወጣ (ምሳሌ ዘርዕ)

መድኃኒታችን በትምህርቱ ለሰማዕያን በጐላ በተረዳ ነገር ይታወቅ ዘንድ ምሳሌን በትምህርት መሣሪያነት ይጠቀምበት ነበር። በእርግጥ ልብ ስለሚነካው ምሳሌያዊ ትምህርቱም ዳዊት አስቀድሞ ዘምሮ ነበር፣ እንዲህ ሲል «እከስት በምሳሌ አፉየ ወእነግር አማሳለ ዘእምትካት - አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ ከቀድሞ የነበረውን ተምሳሌት እናገራለሁ» ብሎ (መዝ ፸፯፥፪)። በባሕር አጠገብ ቆሞ ብዙ ሰዎች በተሰበሰቡበት የሚከተለውን በትምህርት በምሳሌ አስተማረ። አንድ ገበሬ ዘር ሊዘራ ጀመር፤ ዘሩም የተበጠረ የተንጠረጠረ ንጹሕ ዘር ነበር። ሲዘራም አንዳንዱ እርሻውን አቋርጦ የሚያልፈው መንገድ ላይ ወደቀ። መሬቱም በሰው እግር የተጠቀጠቀ፣ የጠበቀ በመሆኑ ዘሩን ከወፎች ዓይን ሊሰውረው የሚችል አፈር ባለመኖሩ ወፎች በቀላሉ ቅመው በሉት። ሌላው ዘር ደግሞ በአለታማ መሬት ላይ ወደቀ። በአለቱ ላይ የነበረው ጥቂት አፈር ከወፎች ዓይን ሰወረውና ወፎች አላገኙትም። በመሆኑም ትንሽ ዝናም ሲዘንብ አፈሩም ራሰ ዘሩም እረጠበና ወዲያውኑ በቀለ። ነገር ግን በቀላሉ የበቀለው ዘር ስር መስደድ የሚያስችለው ቦታ በማጣቱ ጸሐይ በወጣ ጊዜ ስሩን ጸሐይ አገኘው፤ ጭንጫውም አቃጠለው ወዲያው ደረቀ፣ ለፍሬም ለአበባም ሳይበቃ ቀረ። ሌላው ደግሞ በእሾክ መካከል ወደቀ። ወፍም አልበላውም ምድሩም ለም ስለነበር ጸሐይ አላስፈራውም፤ በቀለ አደገ። ነገር ግን እንዳያብብና እንዳያፈራ እሾክ ከቦ አጣበቀው፤ ያለ ፍሬም ቀረ። በአራተኛ ደረጃ ደግሞ የወደቀው ሌላው ዘር በመልካም ቦታ ወደቀ። በቀለ፣ አደገ፣ አብቦ አፈራ፣ አንዱ መቶ ፍሬ፣ ሌላው ስልሳ ፍሬ፣ ሌላው ደግሞ ሠላሳ ፍሬ አፈራ። ይህንን ካለ በኋላ ጆሮ ያለው መስማትን ይስማ አለ መድኃኒታችን።

የምሳሌው ትርጉም፥
ገበሬው (ዘሪው) ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ (የወንጌላ ሐዋርያ) ምሳሌ ነው። ዘሩ የእግዚአብሔር ቃል ነው፤ ጥሩ ዘር ወንጌል ነው፣ አራቱ ልዩ ልዩ ቦታዎች የሰማእያን ልቦና ምሳሌዎች ናቸው።

የመንገዱ ምሳሌ፥ የአንዳንድ ሰዎች ልቦና አውራ መንገድ ይመስላል። በምናምነቱ የተጠቀጠቀ አጋንንት የተመላለሱበት በትዕቢት፣ በእልክ፣ በኃጢአት የጠነከረ እንደ ፈርኦን ልቡና እንቢተኛ የሆነ፣ የተዘራበትን ቃለ ወንጌል መቀበል፣ ከአጋንንት (ከአእዋፍ) መደበቅ

# ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ

ዘሪ ሊዘራ ወጣ (ምሳሌ ዘርዕ) ...

*አንደኛ እሑድ ዘክረምት - የክረምት የመጀመሪያ እሑድ*

የማይሆንለት፣ ቃሉን የማያስገባ የማይደብቅ ነው። በመሆኑም በወፍ የተመሰለው ለማሳት ፈጣን የሆነው ሰይጣን ፈጥኖ ቃሉን ከልባቸው ይወስደዋል (መክ ፲፤፲፱)። ብዙ ሰዎች የወንጌልን ቃል በቤተ ክርስቲያን ሰምተው ወዲያዉኑ በሰይጣን ይነጠቃሉ፤ ምንም እንደሰሙ ይረሱታል። በመሆኑም በሕይወታቸው ለውጥ አያሳዩም። ምን ጊዜም አዲስ አማኝ ይመስላሉ፤ መንፈሳዊ እድገት አይታይባቸውም «አድሮ ጥጃ» ናቸው። እግዚአብሔር ከዚህ ያድነን (ማቴ ፲፫፤፲፰-፳)።

ከጭንጫ ላይ የወደቀው ዘር ምሳሌ፥ (ማቴ ፲፫፤፳-፳፩) በድንጋያማ ወሬት ላይ የተዘራው ቃሉን ሰምቶ ወዲያዉኑ በደስታ የሚቀበል ሰው ምሳሌ ነው። ነገር ግን ስር መስደድ ስላልቻለ ብዙ አልቆየም። ጽንአተ ሃይማኖት አይታይበትም፤ በቃሉ ምክንያት፣ በክርስቶስ ስም ምክንያት፣ በሃይማኖቱ ምክንያት መከራ ወይም ስደት ሲመጣበት ወዲያዉኑ ይሰናከላል። ስለዚህ ለፍሬ ሳይበቃ የሚቀር ሰው ይሆናል። ዛሬም በስሜት የተለወጡ የሚመስላቸው በቤተ ክርስቲያን ቅጽር ግቢ በስብከተ ወንጌል ጊዜ ብቻ ተለውጠው የሚታዩ ጊዜያውያን ክርስቲያኖች ብዙዎች ናቸው። ስር መሰረት ስለሌላቸው ግን ጠላት በቀላሉ ይገረስሳቸዋል። ከዚህ ጌታ ይጠብቀን።

በእሾክ መካከል የተዘራው ዘር ምሳሌ፥ (ማቴ ፲፫፤፳፪-፳፫) ይህ ዘር በቅሏል፤ አድጓል። ያቃተው ማፍራት ነው። ምክንያቱም እሾህ ያዘው። አንድ ሰው ቃሉን ይሰማል፣ ወንጌሉ ይገባዋል፣ ለልቡ ይረዳዋል፤ ሆኖም ግን ለዓለማዊ ሐሳብ፣ ለባለ ጸግነት ስሜት፣ ለሥጋ ክብርና ጥቅም በመገዛት ለቃሉ መታዘዝ ያቅተዋል። በመሆኑም በውስጡ ለእግዚአብሔር ሕግ በሥጋውና በኑሮው ለሥጋ በመገዛት ሁለት ጌታ እየገዛው ያለ ፍሬ ይኖረዋል። ይህንንም ጌታ «በእሾህ መካከል የተዘራው ዘር ቃሉን ሰምቶ በዚህ ዓለም በመጨነቅና በብልጽግና ሐሳብ በመታለል ታንቆ ለፍሬ ያልበቃ ሰውን ይመስላል» ብሎ ተርጉሞታል።

በመልካም መሬት ላይ የተዘራው ዘር ምሳሌ፥ ይህ ቃሉን እየሰማ እየታዘዘ የኖረበትን ዋጋ የተገኘበት ሰው ምሳሌ ነው። ይህ ሰው የጠፋውን ዘር ሊተካ በሚችል ሁኔታ አፍርቶአል ፍሬውም ግሩም ሆኖአል። ወንጌል እንዳለ በጥሩ መሬት ላይ የተዘራው ዘር ግን ቃሉን ሰምቶ የሚያስተውለውን ሰው ይመስላል፤ በእርግጥም ፍሬ ያፈራል፣ አንዱ መቶ፣ አንዱም ስልሳ፣ አንዱም ሠላሳ ፍሬ ሰጠ (ማቴ ፲፫፤፳፫-፳፬)። አምላክ ሁላችንንም ለፍሬ ያብቃን።

## ማስታወሻ

ከዚህ ጋር የሚሄዱ በቅዳሴ ጊዜ የተነበቡ መጻሕፍት ቁርኝት (ተዛምዶ)፥ (ሉቃ ፰፤፬-፰ ። ፩ኛ ቆሮ ፲፭፤፴፭-፶፩ ። ያዕ ፭፤፲፯-፲፰ ። ምስባክ በሙሉ)

ጥቅስ በግእዝ፥ የአርግ ደመናተ እም አጽናፈ ምድር ወገብረ መብረቀ ለጊዜ ዝናም ይዘርዎ ለጊሜ ከመ ሐመድ ወያወርድ በረደ ከመፍተታት ወያህመለምል ሣዕረ ለእንስሳ (ቅዳሴ ኤጲፋንዮስ)

ጥቅስ በግእዝ፥ ደምፁ እገሪሁ ለዝናም ሶበ ይዘንም ዝናም ይፀግቡ ርሁባን (አዝ) ሶበ ይዘንም ዝናም ይትፌስሑ ነዳያን (አዝ) ሰርዐ ሰንበት ለሰብእ እረፍተ (አዝ)
አማርኛ፥ የዝናም ኮቴው ተሰማ (አዝ) ዝናም በሚዘንብ ጊዜ ረሐብተኞች ይጠግባሉ (አዝ) ዝናም በዘነበ ጊዜ ደሃዎች ደስ ይሰኛሉ (አዝ) ሰንበትን ለሰው እረፍት ፈጠረ (አዝ) መዝሙር

በግእዝ፥ አቡሃ ለምህረት ያርሑ ክረምተ በበዓመት
አማርኛ፥ የምሕረት አባት ክረምትን በየዓመቱ ያመጣል።

በግእዝ፥ ያርሑለነ ክረምተ ይገብር ለነ ምህረተ ... ንሴብሕ ወንዜምር ለዘወሀበነ ዝናመ ወጸገወነ ሰላመ
በአማርኛ፥ ለእኛ ክረምትን ያመጣልናል፣ ምህረትንም ያደርግልናል ... እንዘምር እናመስግን ሰላምን ለሰጠ፣ ዝናምን ለሰጠን (ሠላም)

በግእዝ፥ ዘኒ ይዘርዕ እንዘ ይሴፎ ኪያከ፣
ወዘኒ የአርር ብእለ ጸጋከ
ከመ ታወርድ ዝናመ በቃለ ትእዛዝከ
እግዚአ ለሰንበት ስብሐት ለከ

አማርኛ፥ የሚዘራ እንተን ተስፋ አድርጎ ይዘራል
የሚሰበስብም የጸጋህን ሐብት ይሰበስባል
በቃልህ ትእዛዝ ዝናምን ታወርድ ዘንድ
የሰንበት ጌታ ምስጋና ላንተ ይሁን። (ያሬድ)

ወስብሐት ለእግዚአብሔር ... አሜን።

ከመምህር ልዑለ ቃል አካሉ ሥርዓተ አምልኮ ዘኦርቶዶክስ ተዋህዶ ፩ኛ መጽሐፍ የተወሰደ ...
EthiOrthodox e-mail Outreach **EthiOrthodox@AOL.COM**